

# የማር ቆራጩ መሪ በቀል

Zulu folktale

Wiehan de Jager

Mezemir Girma

4

አማርኛ am



ይህ የማር ቆራጩ መሪ የንጌዴና ግንጊሌ የተባለ ገብጋባ ወጣት ታሪክ ነው። አንድ ቀን ግንጊሌ አደን ላይ ሳለ የንጌዴን ጥሪ ሰማ። ግንጊሌ ማርን አስቦ ጎመዠ። ከራሱ በላይ ባሉት የዛፍ ቅርንጫፎች ወፏን እስኪያየው ድረስ እየፈለገ ቆም ብሎ በጥንቃቄ አደመጠ። ‹‹ችክ፣ ችክ፣ ችክ›› በማለት ወደ ቀጣዮቹ ዛፎች እየበረረ ትንሹ ወፍ ጮኸ። ግንጊሌ መከተሉን እርግጠኛ ለመሆን ቆም እያለ እያየ ‹‹ችክ፣ ችክ፣ ችክ›› እያለ ተጣራ።



ከግማሽ ሰዓት በኋላ ከአንድ ትልቅ ሾላ ጋ ደረሱ። ንጌዴ በቅርንጫፎቹ መካከል የሚያደርገውን አጥቶ ቱር ቱር አለ። ካንዱም ቅርንጫፍ ላይ ተረጋግቶ ራሱን ወደ ግንጊሌ ዘንበል አድርጎ ‹‹ይሄውና! አሁን ና! ይህን ያህል ምን አቆየህ?›› የሚለው መሰለ። ግንጊሌ ከዛፉ ስር ምንም ንቦች አልታዩትም፤ ንጌዴን ግን አምኖታል።



ስለዚህ ግንጊሌ የማደኛ ጦሩን ከዛፍ ስር አስቀምጦ ደረቅ እንጨቶችን ለቀመና እሳት አቀጣጠለ። እሳቱ በደንብ ሲቀጣጠል አንድ ረጅም ደረቅ እንጨት በእሳቱ መካከል አደረገ። ይህም እንጨት ሲነድ ብዙ ጭስ የሚወጣው ዓይነት ነበር። በእሳት ያልተያያዘውን የእንጨቱን ጫፍ በጥርሱ ይዞ ዛፍ ይወጣ ጀመር።



ወዲያውኑም የንቦች ድምጽ ጎልቶ ተሰማው። በዛፉ ግንድ ላይ ካለ ቀዳዳ ነበር እየወጡ ያሉት - ከቀፏቸው። ግንጊሌም ከቀፎው ሲደርስ በመቀጣጠል ላይ ያለውን የእንጨቱን ጫፍ ወደ ቀዳዳው ጨመረው። ንቦቹም ተናደው መውጣት ጀመሩ። ጭሱንም ስላልወደዱት በረው ጠፉ፤ ግንጊሌንም ነደፉት!



ንቦቹም እንደወጡ ግንጊሌ እጆቹን ወደ ቀፏቸው አስገባቸው። በጥሩ ማር የተሞላ ብዙ ከባባድ እጭም አወጣ። በትከሻውም ላይ ካነገተው ኮረጆ አስቀመጠውና ከዛፉ መወረድ ጀመረ።



ንጌዴ ግንጊሌ የሚሰራውን እያንዳንዱን ነገር በጉጉት እየተከታተለ ነበር። ለማር ቆረጣ ስለመራው በማመስገን ከያዘው ማር ትንሽ ቆረጥ አድርጎ እንዲሰጠው እየጠበቀ ነበር። ንጌዴ ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ ለመሬት ቀረብ ብሎ ይዘዋወር ጀመር። በመጨረሻም ግንጊሌ ከዛፉ ወረደ። ንጌዴም ከአጠገቡ ካለ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ሽልማቱን ይጠብቅ ጀመር።



ግንጊሌ ግን እሳቱን አጥፍቶ፣ ጦሩን አንስቶና ወፉን ረሰቶ ወደቤቱ መሄድ ጀመረ። ንጌዴም በንዴት ‹‹ቪክ ቶር! ቪክ ቶር›› ሲል ተጣራ። ግንጊሌም ቆም ብሎ ትንሹ ወፍ ላይ አፈጠጠበትና ጮክ ብሎ ሳቀ። ‹‹ትንሽ ማር ፈለገህ ነው፣ ነው አይደል፤ ወዳጄ? አሃ! ግን ስራውን ሁሉ እኮ እኔ ነኝ የሰራሁት፤ የተነደፍኩትም እኔው ነኝ። ታዲያ ከዚህ ማር ለምን እሰጥሃለሁ?›› አለው። ነገደም ተናደደ። እንደዚህ መደረግ አልነበረበትም! መበቀል ግን አለበት።



አንድ ቀን በድጋሚ፣ ከብዙ ሳምንታት በኋላ ግንጊሌ ንጌዴ ማር ሊጠቁመው ሲጠራው ሰማ። ያንን ጣፋጭ ማር አስታውሶ ወፏን በጉጉት ይከተለው ጀመር። ገግንጊሌን በጫካው ጠርዝ ከመራው በኋላ ንጌዴ በአንድ እሾሃማ ዛፍ ስር ለማረፍ ቆመ። ‹‹አሃ፣›› ‹‹ቀፎው በዚህ ዛፍ ላይ መሆን አለበት›› ሲል ግንጊሌ አሰበ። እሳቱን በፍጥነት አያይዞና የሚያያዘውን እንጨት በአፉ ይዞ ዛፉን ይወጣ ጀመር። ንጌዴም ተቀምጦ ይከታተል ጀመር።



ግንጊሌ የተለመደውን የንቦች ድምጽ ለምን እንዳልሰማ እያሰበ ዛፉ ላይ ወጣ። ‹‹ምናልባት ቀፎው በጣም ጥልቅ ቦታ ላይ ይሆናል ያለው›› ሲል ለራሱ አሰበ። ወደሌላ ከፍ ወዳለ ቅርንጫፍ ላይ ወጣ። ያገኘው ነገር ግን ቀፎ ሳይሆን ፊት ለፊት የመጣችበትን ነብር ነበር! ነብሯ እንቅልፏን ሳታስበው ስላቋረጣት በጣም ተናደደች። ዓይኖቿን ጠበብ አድርጋ፣ አፏን ከፍታ፣ ትላልቅና ሹል ጥርሶቿን አገጠጠችበት።



ነብሯ ለቀም ሳታደርገው ግንጊሌ ከዛፉ በፍጥነት መውረድ ጀመረ። በፍጥነቱም የተነሳ አንዱን ቅርንጫፍ ስቶት መሬት ላይ ክፉኛ ወድቆ ቁርጭምጭሚቱ ዞረ። በተቻለው መጠን በፍጥነት እያነከሰ ሄደ። ዕድሉ ረድቶት ነብሯ እንቅልፍ ስለተጫናት አላሳደችውም። ንጌዴ፣ የማር ቆራጩ መሪ፣ በቀሉን ተበቅሏል። ግንጊሌ ም ትምህርት ቀስሟል።



ስለዚህ የግንጊሌ ልጆች የንጌዴን ታሪክ ሲሰሙ ለዚያ ትንሽ ወፍ አክብሮት አላቸው። ማር በቆረጡ ቁጥር ለማር ቆራጩ መሪ ከነእጩ ብዙ ቆረጥ አድርገው መስጠታቸውን ያረጋጣሉ።

# Global Storybooks

globalstorybooks.net

## የማር ቆራጩ መሪ በቀል

Zulu folktale

Wiehan de Jager

Mezemir Girma

CC BY